# የቆላስይስ መልዕክት (28)

## የመንደርደሪያ ሃሳብ

የሰው ልጅ በእውቀትና በቴክኖሎጂ እየተራቀቀ የመጣበት አሁን እንዳለንበዝ ዘመን እንደሌለ ለማንም ሰው ግልጽ ነገር ነው፡፡ ከዚህም ሁኔታ የተነሳ ሰው የራሱን ችግር ለመፍታት ራሱ እንደሚችልና ሌላ የእግዚአብሄርም ሆነ ማናቸውም ተጨማሪ ሃይል እንደማያስፈልገው አምኖ የተቀበለበት ጊዜ ሲሆን ይህ ልናጠና ያለነው የቆላስይስ መልዕክት በዚህ አቅጣጫ በማያሻማ መንገድ ክርስቶስ ሁሉን በሁሉ እንደሆነና የጥበብም ሁሉ ምንጭ እርሱ መሆኑን ያሳየናል፡፡

የቆላስይስ መልዕክት ሐዋርያው ጳውሎስ በሮማ እስር ቤት ሆኖ ከጻፋቸው አራት መልዕክቶች አንዱ ሲሆን የተጻፈውም ከ60-62 ዓ.ም አካባቢ እንደሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች ይናገራሉ፡፡ ይህ መልዕክት ዋነኛ ትኩረቱን ያደረገው የክርስቶስን እውነተኛ ማንነት በማወጅ ላይ ነው፡፡ ከቆላ 1፡4፣9 እና 2፡1 እንደምናየው ጳውሎስ ስለ ቆላስይስ ቤተ ክርስትያን መስማት እንጂ እንዳላያቸው እንረዳለን፡፡

በአብዛኛዎቹ በጳውሎስ መልዕክቶች እንደሚታየው የዚህ መልዕክትም ዋና አከፋፈል ሲታይ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምዕራፎች ዶክትሪን ላይ ያተኮሩ ሲሆኑ፤ የተቀሩት ሁለቱ ደግሞ ተግባራዊ እንዴት ማድረግ እንደሚኖርብን የሚያስተምሩን ናቸው፡፡ ይህ የቆላስይስ መልዕክት ከኤፌሶን መልዕክት ጋራ ተቀራራቢነት ይታይበታል፣ ሆኖም ኤፌሶን በክርስቶስ ቤተ ክርስትያን ላይ ሲያረኩር ቆላስይስ ደግሞ የቤተ ክርስትያን ክርስቶስ ማን እንደሆነ በማሳየት ላይ ትኩረት ያደርጋል፤ ማለትም የኤፌሶን መልዕክት ክርስቶስ የእኔ የሚላት ቤተ ክርስትያን ምን እንደምትመስል የሚያሳይ ሲሆን የቆላስይስ መልዕክት ደግሞ ቤተ ክርስትያን የእኔ የምትለው ክርስቶስ ማን እንደሆነና ምን እንደሚመስል በግልጽ ያሳያል፡፡ ስለዚህም ኤፌሶን በአካሉ(ቤ/ክ) ላይ ትኩረት አድርጓል ብንል፤ ቆላስይስ ደግሞ በራሱ(ክርስቶስ) ላይ አተኵሯል ማት እንችላለን፡፡

ሐዋርያው ይህንን መልዕክት የጻፈባቸው ቢያንስ ሶስት ምክንያቶችን መጥቀስ ይቻላል፣ የመጀመሪያው ጳውሎስ ስለነዚህ ቅዱሳን እንደሚገደው ለማሳየት (1፡3-4፤ 2፡3) ሁለተኛው ወደ ቀድሞው አይነት ህይወታቸው እንዳይመለሱ ለማስጠንቀቅ (3፡5)ና በሶስተኛ ደረጃ ደግሞ በቤተ ክርስትያን አካባቢ ለተዘራው የስህተት ትምህርት መልስ ለመስጠት ነው (2፡4-23)፡፡ ጳውሎስ የሐሰት ትምህርቱን ዓይነት ሲዘረዝር በብዙ አይታይም፤ ነገር ግን የክርስቶስን ትክክለኛውን ማንነት በማሳየትና በማስተማር ላይ ነው ያተኮረው፡፡ የተለያዩ የሐሰት ትምህርቶችን በማጥናት ላይ ጊዜን ከማጥፋት ክርስቶስንና ቃሉን እንደሚገባ በመረዳት ላይ ማተኮር በቂ መልስ ሊሆነን እንደሚችል ከሐዋርያው ትምህርት ልንቀስም እንችላለን፡፡

አቻና እኩያ የማይገኝለትን የክርስቶስን ማንነት ለማጥናት በምንሰበሰብባቸው ከፊታችን ባሉት ቀናት ሁሉ እግዚአብሄር ከማናቸውም ጊዜ በላይ የልብ ዓይኖቻችንን እንዲከፍትልን በጸሎት ልንቀርብ ይገባናል፡፡

# ጥናት አንድ ቆላስይስ 1፡1-14 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ሰላምታ አቅራቢዎቹ ጳውሎስና ጢሞቲዎስ ሲሆኑ፤ ጳውሎስ ደግሞ ራሱን ያስተዋወቀው በእግዚአብሄር ፈቃድ ሐዋርያ አድርጎ ነው፡፡ የቆላስያስ አማኞችን የጠራቸው፡ ቅዱሳን፣ ታማኝና ወንድሞች በማለት ነው፡፡
2. በቁ3 ላይ የሚጸልዩት ሰዎች ቁጥር ከአንድ ሰው በላይ መሆኑን እርግጠኞች ነን፡፡ ሌሎቹ ክፍሎች ላይ ጳውሎስ የሚጸልየው በግሉ እንደሆነ ስናይ በዚህ ክፍል ግን ከሌሎች ሰዎች ጋራ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ከዚህ ሐዋርያ ልምምድ ልንማር የምንችለው ጸሎት በግል እንዲሁም በህብረት መለማመድ የሚኖርብን ነገር መሆኑን ነው፡፡
3. የምስጋናው ምክንያቶች፡ በክርስቶስ ስላላቸው እምነትና፣ ለቅዱሳን ስላላቸው ፍቅር ነው፡፡ ለነዚህ ምንጭ ሆኖ የቀረበውም ነገር በሰማይ ካላቸው ተስፋ የተነሳ መሆኑ ነው፡፡
4. ወንጌልን ከሰሙበትና ጸጋውን በእውነት ከተረዱበት ቀን አንስቶ ነው፡፡ ወንጌልን እንዲሰሙ ምክንያት የሆናቸው ሰው ኤጳፍራ ነው፡፡
5. ኤጳፍራ ታማኝ አገልጋይ ነው፣ አብሮ መስራት የሚችል ነው፣ ተወዳጅ ባህርይ አለው፣ የተረዳውን ያካፍላል/ያስተምራል፣ በሰዎች ያለውን መልካም ነገር ማየት ይችላል፡፡ እነዚህ ባህርያት የጌታን አገልጋይ ፍሬያማ የሚያደርጉት ስለሆኑ ልንጠማቸው ያስፈልጋል፡፡
6. በቁ3 ላይ ያለው ጸሎት በጊዜው እየተለማመዱት ስላሉት በጎ ፍሬ ምስጋና ሲሆን፤ ቁ9 ላይ ያለው ግን በተጨማሪ በህይወታቸው እንዲታይ በሚፈልጋቸው ነገሮች ላይ ያተኮረ ሃሳብ ነው፡፡ ከዚህ የምንማረው አንድ ደረጃ ስንወጣ መውጣት የሚኖርብን ሌላ ደረጃ መኖሩንና በከርስትና ህይወት እድገት መቆም የሌለበት ነገር እንደሆነ ነው፡፡
7. በመልካም ሥራ ፍሬ ማፍራት፣ እግዚአብሄርን በማወቅ ማደግ፣ ታላቅ ጽናትና ትዕግስት መለማመድ፣ በሃይሉ መበርታት፣ ደስ መሰኘት፣ በቁዱሳን ርስት ተካፋይ ያደረገንን አብን ማመስገን፡፡
8. እያንዳንዱ የየራሱን ሃሳብ ይስጥበት፡፡

# ጥናት ሁለት ቆላስይስ 1፡15-29 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እርሱ እያለ የሚናገረው በቁ13 የጀመረውን ኢየሱስን ማለቱ ሲሆን በእርሱ ተፈጠሩ ተብለው የተዘረዘሩት፡ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ… ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሯል። ሁሉ ስለሚል በእርሱ ያልተፈጠረ ምንም ነገር እንደሌለ እንረዳለን።
2. አምሳል የሚለው ቃል ቢያንስ ሶስት ሃሳቦችን ያካትታል። መመሳሰልን (ሙሉ በሙሉ እግዚአብሄርን መምሰሉን ዕብ 1፡3)፣ መወከልን (ክርስቶስ ለእኛ እግዚአብሄርን ይወክልልናል ዮሐ 14፡9) እና መግለጥን (ክርስቶስ እግዚአብሄርን ለእኛ ይገልጥልናል ዮሐ 1፡18) በተጨማሪ ቆላ 1፡19ኝን ተመልከት ከፍጥረት በኩር ማለቱ ደግሞ መፈጠሩን ሳይሆን ሊነግረን የፈለገው የጊዜ ቅድሚያን ዘጸ 4፡22፣ ሮሜ 8፡29 ወይም በሥልጣን የበላይነትን መዝ 89፡27፣ ዕብ 1፡6 ሊጠቁመን ነው።
3. ቤተ ክርስትያን የክርስቶስ አካል ስትሆን፤ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስትያን ራስ ነው። በአጭሩ አነጋገር ለእኛ አካል የሚሆን ማናቸውም ትዕዛዝና መመሪያ የሚመጣው ከራሳችን እንደሆነ ሁሉ የቤተ ክርስትያን አዛዥና መሪ ክርስቶስ መሆኑን በእርሱ ሃሳብም መተዳደር እንደሚኖርባት እንረዳለን።
4. በሮሜ 12፡4-8 ላይ አካልን የተጠቀመው በቤተ ክርስትያን ውስጥ አንድነትና ልዩነቶች እንደሚኖሩ ለማስተማር ሲሆን፤ በዚህ ክፍል ውስጥ ግን ክርስቶስ ከማንኛውም ክርስትያን የበላይነት እንዳለው ሁሉም በእርሱ ስልጣን ሥር እንደሆነ ለማስተማር ነው።
5. ‹‹…ሁሉም ነገር ለእርሱና በእርሱ ተፈጥረዋል።›› ቆላ 1፡16 ከሁሉ የሚጎላ ይመስለኛል ነገር ግን ሌሎችም ስለሚኖሩ የተለያዩ ሃሳቦችን ለመስማት ጊዜ ውሰዱ።
6. ይህ ክፍል የሚናገረው ስለአማኞች ነው። እነዚህ ሰዎች ቀድሞ ክፉዎች፣ ከእግዚአብሄር የተለዩና በሃሳባቸውም ጠላቶቹ ነበሩ። አሁን ግን እነዚሁ ሰዎች ነውር የሌለባቸው፣ ነቀፋ የሌለባቸውና ቅዱሳን አድርጎ ክርስቶስ አስታርቋቸዋል።
7. አንደኛው ስለ አካሉ ማለትም ስለ ቤተክርስትያን መከራን ይቀበላል፤ ሌላው ደግሞ ቃሉን ይሰብካል። ቃሉን በተመለከተ የተነገሩት ደግሞ፤ ቃሉ ለዘመናት ተሰውሮ እንደነበረና አሁን ግን ለቅዱሳኑ እንደተገለጠ ተነግሮናል።
8. ጳውሎስ ግብ አድርጎ የሚለፋለት ነገር እያንዳንዱን ሰው በክርስቶስ ፍጹም አድርጎ ማቅረብ ነው። ይሰብካል፣ ይመክራል፣ ያስተምራል። እግዚአብሄር በአማኝ ህይወት ውስጥ ሆኖ ሰዎችን ወደደህንነት እንዲመጡ እንደሚለፋና እንደሚሰራ ከዚህ ክፍል እንመለከታለህ ስለዚህም ከእግዚአብሄር ጋራ አብረን የምንሰራ ነን የሚለውን ግልጥ ያደርግልናል።
9. አሁን የምናየው ነገር ሁሉ እርሱ አጽንቶ ባያቆመው በሥርዓት ሊቆም አይችልም ነገረ። ጌታችን በዙፋኑ ላይ እስካለ ድረስ ምድር ብትነዋወጥና ማናቸውም ነገር ቢሆን እርሱ ካቀደው ነገር ውጭ ሊመጣ ስለማይችል ልንጨነቅ አይገባም።

# ጥናት ሶስት ቆላስይስ 2፡1-12 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንዲያውቁት የፈለገው ነገር እየተጋደለላቸው እንደሆነ ሲሆን ተጋድሎውም ለእነርሱ ብቻ ሳይሆን በሎዶቅያ ላሉትና ሌሎችንም ያልተጠቀሱትን ሁሉ ጨምሮ ነው፡፡
2. በዚህ ክፍል እጋደላለሁ ሲል እነርሱን በተመለከተ እያደረገ ያለውን ጥረትና ልፋቱን ለማመልከት ነው፡፡ ተጋድሎው የሚያካትታቸው ነገሮች በመጀመሪያ ደረጃ በጸሎት መጋደሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በእስር ላይ ሆኖ ይህንን መልዕክት ማቀናበሩ፣ ሰዎች ሲያገኝ መልዕክት ማስተላለፉና ሌሎችንም ነገሮች ሊጨምር ይችላል፡፡
3. ጳውሎስ ለተጋድሎው ምክንያት አድርጎ የሚሰጣቸው ነገሮች፡- የቅዱሳኑ ልብ እንዲበረታታ፣ በፍቅር እንዲተሳሰሩና የእግዚአብሄር ምስጢር የሆነውን ክርስቶስን እንዲያውቁ ነው፡፡ ክርስቶስን እንደሚገባ እንዲያውቁት የፈለገው የተሰወረ የጥበብና የእውቀት ሃብት ሁሉ የሚገኘው በእርሱ ውስጥ ስለሆነ ነው፡፡
4. ማንም ሰው ንግግሩን በማሳመር ይህንን በተመለከተ ቢናገራቸው እንዳይታለሉ ነው፡፡ ከዚህ ድርጊቱ መማር የምንችለው፣ አማኞች እንዳይስቱ የሐሰት ትምህርትን ምንነት ማስተማር ሳይሆን ትክክለኛና እውነት የሆነውን የወንጌልን ቃል ማስተማር ከሐሰት ትምህርት እንደሚከላከል ነው፡፡
5. አንደኛው በሥርዓት መኖር ሲሆን ሌላው ደግሞ በክርስቶስ ላይ ያላቸው የጸና እምነት ነው፡፡ እነዚህ ክርስትያኖች በጌታ እናምናለን ብለው የአፍ እምነት ሳይሆን ለእምነታቸው ማረጋገጫ የሚሆን ዓይነት ኑሮ ስለሚታይባቸው መልካም ምስክርነት ያለው ህይወት አላቸው ማለት እንችላለን፡፡
6. ክርስቶስን እንደተቀበሉ በእርሱ እንዲኖሩ፣ በእርሱ እንዲተከሉ፣ በእርሱ እንዲታነጹ፣ በእምነት እንዲጸኑና የተትረፈረፈ ምስጋና እያቀረቡ እንዲኖሩ፡፡
7. በክርስቶስ ሙሉ እንደሆኑ፣ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ ተገርዘዋል፣ በመገረዝ የሥጋን ሃጥያታዊ ባህርይ አስወግደዋል፣ በጥምቀት ከእርሱ ጋራ ተቀብረዋል፣ ከእርሱ ጋራ ደግሞ ተነስተዋል፡፡
8. በ2ኛ ጴጥ 1፡3 እና በቆላ 2፡3 እንደምናነበው ለህይወትና እግዚአብሄርን ለመምሰል ሁሉ የሚያስፈልገው ክርስቶስ ስለሆነና እርሱም በውስጣችን ስላለ ከአሁን በኋላ የሚያስፈልገን የእግዚአብሄር ስጦታ የሆነውን ጠንቅቀን ማወቅ ለሁሉም ነገር መልስ ስለሚሆነን ነው፡፡ የተቀረውን መልስ እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ ይስጥበት፡፡

# <u>ጥናት አራት ቆላስይስ 2፡13-23 (ለመሪው የተዘጋጀ)</u>

1. ቀድሞ ሙታን የነበርንባቸው ምክንያቶች አንደኛው በደላችን ሲሆን ሌላው ደግሞ የሥጋችንን ሐጥያታዊ ባህርይ አለመገረዛችን ናቸው፡፡ እግዚአብሄር ለዚህ መፍትሄ አድርጎ የተጠቀመው የክርስቶስን መስቀል ነው፡፡
2. ሃጥያታችንን ሁሉ ይቅር አለን፣ ሲቃወመን የነበረውን የእዳ ጽህፈት በመስቀል ቸንክሮ ከመንገድ አስወገደው፣ የአለቆችንና የባለሥልጣናትን ማዕረግ ገፈፈ(ሞትን፣ ሰይጣንንና ሰራዊቱን ሁሉ)፡፡
3. በቁ13-15 ያሉት ነገሮች እግዚአብሄር ለደህንነታችን የሰራቸው ሥራዎች ሲሆኑ በቁ16-17 ላይ ግን ሰዎች ለመንፈሳዊነታችን መስፈርት አድርገን እንድንፈጽማቸው የሚሞክሩቸው ነገሮች ናቸው፡፡ ጳውሎስ ይህንን አስመልክቶ ለክርስቶስ ጥላ ስለሆኑና አሁን ግን እርሱ ስለተገጠ በጥላው አንመላለስም ነው ሃሳቡ፡፡
4. የመላዕክት አምልኮ አጉል ትህትና የሚሆንበት ምክንያት፤ እኔ የማልረባ ሰው ስለሆንኩ በቀጥታ ወደ እግዚአብሄር መቅረብ አልችልም፤ ስለዚህም በመላዕክት በኩል መቅረብ እችላለሁ ብሎ ማሰብ ሊሆን ይችላል፡፡ እግዚአብሄር በቀጥታ ወደ እርሱ እንድንቀርብ በመስቀል መንገድ ስላዘጋጀልን ያንን ከመጠቀም ይልቅ የራሳችንን መንገድ ማዘጋጀታችን ከእርሱ ይልቅ እኔ አውቃለሁ የሚል ከትህትና ይልቅ ትዕቢት ሆኖ ይገኛል፡፡
5. ራሱን ከመጠን በላይ ይከባል፣ ይታበያል፣ ራስ ከሆነው ጋራ ግንኙነት የለውም፡፡ ‹‹ራስ ከሆነው ጋራ ግንኙነት የለውም›› ያለበት ምክንያት ወደ አብ ሊደረስ የሚችልበት አንድ መንገድ ክርስቶስ ስለሆነና እርሱ ግን ለራሱ የመረጠው መንገድ ሌላ ስለሆነ ከክርስቶስ ጋራ ግንኙነት ሊኖረው አይችልም፤ ክርስቶስ ከሌላ ጋራ መዳበል አይችልምና፡፡
6. የዚህ ክፍል ትኩረት በሰዎች ትዕዛዝና ትምህርትን በመጠበቅና ባለመጠበቅ ላይ ነው፡፡ አትያዝ፣ አትቅመስ፣ አትንካና የመሳሰሉት ህግጋት ሰው ሰራሽ ስለሆኑና እኛ ግን ከክርስቶስ ጋራ መሞታችን ለሃጥያት መሞት መሆኑን በመገንዘብ ለዚያ እውነት የመኖር ሃላፊነት ብቻ እንዳለብን እንድንገነዘብ ነው፡፡
7. እነዚህ ነገሮች በህይወታችን ሊፈጥሩ የሚችሏቸው ስሜቶች፡ የአምልኮ ስሜት፣ አጉል ትህትና፣ ሰውነትን መጨቆን እውነትም ጥበብ ያላቸው ይመስላሉ፡፡ አንድ ግን ማድረግ የማይችሉት የሥጋችንን ልቅነት ለመቆጣጠር ሊረዱን አይችሉም፡፡
8. የሰዎችን መንፈሳዊነት ሰው ሰራሽ ህግጋትን በመጠበቅ ላይ ከመሰረትነው በቆ2፡10 ላይ ‹‹በክርስቶስ ሙሉ ሆናችኋል›› የሚለውን እውነት ፉርሽ በማድረግ በራሳችን ማሟላት ያለብን ነገር እንዳለ ማመን ይሆናል፡፡ የተቀሩትን ሃሳቦች ሁላችሁም ሃሳባችሁን በመስጠት ተወያዩባቸው፡፡

## ጥናት አምስት ቆላስይስ 3፡1-11 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እንዲያደርጉ የጠየቃቸው የመጀመሪያው በላይ ያሉ ነገሮችን እንዲሹ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሃሳባቸው በላይ ባለው ነገር ላይ እንዲሆን ነው፡፡ ለዚህም የሰጣቸው ምክንያቶች፡ ከክርስቶስ ጋራ ስለተነሱ፣ ህይወታቸው ከክርስቶስ ጋራ ስለተሰወረና፣ ክርስቶስ ሲገለጥ እነርሱም ከክርስቶስ ጋራ ስለሚገለጡ ማለትም ስላላቸው ተስፋ ማለት ነው፡፡
2. በ2፡13 ላይ በሃጥያታችን ምክንያት ስለመጣብን የሞት አይነት የሚናገር ሲሆን በ3፡3 ላይ የምናየው ግን ከሃጥያት ባርነት ነጻነትን ለማግኘት ከክርስቶስ ሞት ጋራ ስለተባበርነው ሞት ነው፡፡
3. በ3፡3 ላይ ያለውና ‹‹ሞታችኋል›› የሚለን በእግዚአብሄር አይን የምንታይበትና ራሳችንም እንደተፈጸመ እንድናምን የሚጠበቅብን እውነት ሲሆን በ3፡5 ላይ ያለው ግን በእምንት የተቀበልነውን በተግባር እንድንተረጉም የሚጠይቀን ክፍል ነው፡፡ በተጨማሪ ሮሜ 6፡5-14ትን ማንበብ ይረዳል፡፡
4. በ3፡1-4 ውስጥ ክርስቶስ የሚለው ስም አራት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ከመሞታችን ጋራ፣ ከመነሳታችን ጋራ፣ የት እንደሚገኝና ተመልሶ እንደሚመጣ አስመልክቶ ሲናገር ነው ስሙ የተጠቀሰው፡፡ ይህ ስም ከዚህ ምንባብ ውስጥ ቢወጣ፤ ሞቶ መነሳት የለም፣ በበሰማይ መቀመጣችን አይኖርም፣ ተስፋ የሞላበት ህይወት አይኖረንም፤ በአጠቃላይ ክፍሉ ትርጉም የማይሰጥ ይሆን ነበረ፡፡
5. ቁጣው የሚመጣበት ምክንያት በቁ5 ላይ የተዘረዘሩትን ነገሮች አማኞች በህይወታቸው መለማመድ አላቆም ሲሉ ነው፡፡ በመፍትሄነትም ሃዋርያው ያቀረበው ሃሳብ ምድራዊ ምኞቶቻችንን መግደል ነው፡፡
6. በ1-4 ላይ ልባችንና ሃሳባችን በሰማያዊ ነገር ላይ መሆን ከጀመረ በ5-11 ላይ ያለውን ለመፈጸምና እነዚህን ምኞቶቻችንን ለመግደል መሰረት ይኖረናል ማለት ነው፤ ይህ ካልሆነ ግን ልባችን በምድራዊ ነገር ላይ ሆኖ እያለና አዕምሯችንም የዓለምን ነገር ዘወትር እያሰላሰለ ካለንበት ማጥ መውጣት የማይሆን ነገር ይሆናል፡፡ ሮሜ 12፡1-2ት ይነበብ፡፡
7. ሐዋርያው ይህንን ለመግለጥ የተጠቀመው ‹‹አሮጌ ልብስን ማውለቅና፤ አዲስን ልብስ መልበስ›› የሚለውን አነጋገር ነው፡፡ ልብስን አውልቆ ከማስቀመጥ ይልቅ አውልቆ መጣል የሚለውን የተጠቀመው፤ አውልቀን ያስቀመጥነው ነገ ታጥቦ፣ ተተኩሶ መልሶ ይለበሳል፤ የተጣለ ልብስ ግን ተመልሶ የሚለበስ አይደለም፡፡ ይህንን ለመረዳት የቆሸሸ ልብስ ማጠራቀሚያ ውስጥ የሚገባ ልብስና የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ውስጥ የምናደርጋቸው ነገሮች እንደሚለያዩ ማሰብ ይረዳል፡፡
8. በቆላ ‹‹የፈጣሪውን መልክ እንዲመስል›› የሚለው ሃሳብ በሮሜ ደግሞ የእግዚአብሄር ለአማኞች ያለውን የዘላለም ዕቅድ ሲናገር የልጁን መልክ እንዲመስሉ እንደሆነ ይነግረናል፡፡ ስለዚህ የእነዚህ ሁለት ክፍሎች መመሳሰል ይህ አዲሱ ሰዎችን ክርስቶስን በማወቅ እየታደሰ (ፊሊ. 3፡10 ተመልከት) ክርስቶስን ወደመምሰል ይደርሳል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ 3፡11 ከዚህ አንጻር ሊኖረው የሚችለው ትርጉም፤ በክርስቶስ ያለን ሁላችን ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የኑሮ ሁኔታና የመሳሰለው ነገር ሳይኖር መጨረሻችን ክርስቶስን መምሰል እንደሆነ ነው፡፡
9. ሰው በክርስቶስ ሞቶ ከተነሳ፤ በ2ኛ ቆሮ5፡17 መሰረት አዲስ ሰው ስለሆነ፤ በአዲስ መሻትና በአዲስ አስተሳሰብ የሚመላለስ ሰው አረማመዱና አኗኗሩም ልቡ የሚሻውንና አዕምሮው የሚያስበውን ያንጸባርቃል ማለት ነው፡፡ ሌላው ጥያቄ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ይመልስ፡፡

## ጥናት ስድስት ቆላስይስ 3፡12-17 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. እነዚህ ቅዱሳን እንዲለብሱ የታዘዙት ርህራሄን፣ ትዕግሥትን፣ ትህትናን፣ ጨዋነትንና ትዕግሥትን እንዲለብሱ ነው፡፡ ‹‹ለብሳችኋል›› የሚለው የሚያሳየን አሮጌው ነገር አልፎ በክርስቶስ አዲስ ሰው መሆናችንን (የማንነታችን መለወጥ) ሲሆን፤ ‹‹ልበሱ›› የሚለው ግን በተግባራችን ላይ ማለትም እለት በእለት በህይወታችን አዲስ መሆናችንን የምናረጋግጥበት መንገድ ነው፡፡
2. እነዚህ አማኞች የተቀደሱ ናቸው፣ በእግዚአብሄር የተወደዱ ናቸው፣ የእግዚአብሄር ምርጦች ናቸው በማለት ይነግረናል፡፡ እነዚህ አባባሎች ምን ያህል በእግዚአብሄር ዘንድ የተከበርንና ግንኙነታችን ልዩ አይነት መሆኑን ያሳየኛል
3. በየእለቱ የሚከናወን ተግባር መሆኑን አያለሁ፡፡ እነዚህ ባህርያትም አንድ ቀን ጠለቅ አድርገን የሚያበቃ ሳይሆን ዘወትር በህይወታችን እያደጉና እየጨመሩ የሚሄዱ ነገሮች ስለሆኑ የየእለት ነገሮች መሆናቸው ያመሳስላቸዋል፡፡
4. እርስ በእርሳችሁ ተቻቻሉ ሲል፤ በመጀመሪያ ደረጃ እያንዳንዱ አማኝ ፍጹም እንዳልሆነና የማንስማማበት፣ ደስ የማያሰኘንን ነገር ሊያደርግ እንደሚችል ይጠቁመናል፡፡ በተጨማሪ የሚያመለክተን ነገር ሁላችን የተለያየ background ስለለን ባህርያችን፣ አነጋገራችን፣ አስተሳሰባችንና ሌሎችም ልዩነቶች ስለሚኖሩን ካልተቻቻልን እንደምንጠፋፋ ይነግረናል፡፡
5. ለያንዳንዱ የተለያየ ሊሆን ስለሚችል የራሱን ይናገር፡፡ በአጠቃላይ በክርስትያኖች መሃል ስንቸገርባቸው የማያቸው በእኔ አመለካከት፤ አለመቻቻልና ይቅር አለመባባል ናቸው፡፡ ትህትናን እንደ ክርስቶስ ብንለብስ ለአብዛኛው ችግራችን መፍትሄ ይሆናል ብዬ እገምታለሁ፡፡
6. እርስ በእርስ ፍቅር ካለን የሌላውን ስህተትና ድክመት በፍቅር እየሸፈንን የማለፍ ሃይል ይኖረናል፡፡ ሌላው ሁሉ እያለን ፍቅር ግን ከሌለን ከንቱ እንደሆነ በ1ኛ ቆሮ 13፡1-3 ላይ እናነባለን፡፡
7. እያንዳንዱ ለራሱ የሚመቸውን ሳይሆን ሰላም እንዳይደፈርስ የተቻለውን ሁሉ ቢያደርግ ዛሬ የሚታየው አንዱ ሌላውን ከማፍረስ ይልቅ መተናነጽ ይሆን እንደነበረ እገምታለሁ፡፡ ይህ ማለት ግን ሰዎች ሲስቱ ዝም ብሎ ማለፍ ሳይሆን የእግዚአብሄር ቃል እንደሚናገረው እውነቱን በፍቅር መናገር ያስፈልጋል፡፡
8. በዚህ ክፍል የታዘዙት፡ የክርስቶስ ቃል በሙላት እንዲኖርባቸው፣ እርስ በእርስ በጥበብ ሁሉ እንዲማማሩ፣ እንዲመካከሩና በልባቸው ለእግዚአብሄር እንዲዘምሩ ነው፡፡ እነዚህን ሁሉ ለማድረግ የክርስቶስ ቃል በልባችን ውስጥ በሙላት መኖሩ ወሳኝነት እንዳለው እናያለን፡፡
9. ሁሉም እንዲሳተፍና ሃሳብ እንዲሰጥ በማደፋፈር ሰፋ ያለ ውይይት ይደረግበት፡፡

# ጥናት ሰባት ቆላስይስ 3፡18-4፡1 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. የተነገራቸው ለባሎቻቸው እንዲታዘዙ ሲሆን የሰጣቸው ምክንያትም በጌታ ዘንድ ተገቢ ነገር እንደሆነ ነው፡፡
2. ባሎች የታዘዙት ደግሞ ሚስቶቻቸውን እንዲወዱና መራራ እንዳይሆኑባቸው ነው፡፡ ‹‹መራራ አትሁኑባቸው›› “Don’t be harsh with them” ሲል ምናልባትም በ1ኛ ጴጥ 3፡7 ላይ እንደተናገረ በንግግርም ሆነ በምግባር መንከባከብና በተለያየ መንገድ እንዲያብቡ መርዳት እንጂ በቃላት ማጣጣልና ዝቅ ማድረግ እንደማይኖርብን ለማስተማር ይሆናል፡፡
3. ለወላጆቻቸው በሁሉም ነገር እንዲታዘዙና የሚታዘዙበትም ምክንያት ደግሞ ጌታን ደስ የሚያሰኝ ነገር ስለሆነ ነው፡፡ እኛም ከዚህ ልንማር የምንችለው ለልጆች እንደተነገረው እየመረጥን ሳይሆን አባታችን ያዘዘንን ሁሉ መታዘዝ እንደሚኖርብንና ይህንንም የምናደርገው አባታችንን ደስ ለማሰኘት ነው፡፡
4. አባቶች ደግሞ የታዘዙት ልጆቻቸውን እንዳያስመርሯቸው ነው፡፡ ልጆቻቸውን በማስመረር ከቀጠሉ ግን ልጆቻቸው ተስፋ ይቆርጣሉ ነው የሚለው ቃሉ፡፡ ቤተሰብ ልጆቹን ሁልጊዜ ከፉ ባደረጉት ላይ ብቻ በማተኮር በየቀኑ መነዛነዝ ሲበዛና መልካሙን እያየን ሳናበረታታ ስንቀር ብሞክርም ዋጋ የለውም ብለው ተስፋ ወደመቁረጥ ሊደርሱ ይችላሉ፡፡
5. በዚህ ክፍል የተጠቀሱት መንገዶች አንዱ ሰው ለማስደሰትና ለታይታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቅን ልብና ጌታን በመፍራት የሚደረግ ነው፡፡ እኛ የታዘዝነው ሁለተኛውን እንድንከተል ነው፡፡
6. ጌታን እንደሚያገለግሉ ሆነው ማገልገል የሚኖርባቸው ምክንያቶች አንደኛው ብድራት የሚቀበሉት ርስት ስላለና ሌላው ደግሞ በዚህ የሚበድል የእጁን ዋጋ ስለሚያገኝ ማለትም  በሰራው ሥራ ስለሚጠየቅበት ነው፡፡
7. የሙሉ ጊዜ አገልጋይ የሚያሰኘው የተሰማራበት የስራ ዓይነት ሳይሆን ስራውን በምን መንገድ እንደሚሰራ ነው፡፡ በልምድ ሙሉ ጊዜ አገልጋይ የምንላቸው በወንጌል አገልግሎት ላይ ብቻ የተሰማሩትን ሲሆን በዚህ ሁኔታ ግን ማንኛቸውንም ዓይነት ሥራ የሚሰሩ ሁሉ ጌታን እንደሚያገለግሉ አምነው የሚሰሩ ሁሉ የሙሉ ጊዜ የክርስቶስ አገልጋዮች መባል ይችላሉ፡፡
8. ጌቶች የታዘዙት ደግሞ አገልጋዮቻቸውን በፍትህና በቅንነት እንዲያስተዳድሩ ሲሆን የሰጣቸው ምክንያትም እነርሱም በሰማይ ጌታ ስላላቸው ነው፡፡
9. መጽሐፍ ቅዱሳችን የስልጣን ተዋረድ እንዳለ የተናገራቸው ቢያንስ አራት ድርጅቶችን እናያለን፤ እነዚህም፡ በቤተሰብ፣ በሥራ ቦታ፣ በቤተ ክርስትያንና በመንግሥት ናቸው፡፡ ዛሬ የሚጠናው ጥናት ያተኮረባቸው ሁለቱ ድርጅቶች፤ ቤተሰብና የሥራ ቦታ ናቸው፡፡ የተቀሩት መልሶች እያንዳንዱ ይመልስ፡፡

# ጥናት ስምንት ቆላስይስ 4፡2-18 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ቁ2-4 ትኩረት ያደረገው በጸሎት ላይ ነው፡፡ ቁ2ትን በማንበብ ስለጸሎት ልንረዳ የምንችላቸው ነገሮች፤ ሀ) ጸሎት ትዕዛዝ እንደሆነ እናያለን፣ ለ) ጸሎታችን በትጋት መሆን አለበት፣ ሐ) ጸሎት በንቃት መደረግ ያለበት ነገር መሆኑን እናያለን፣ መ) ጸሎት ምስጋናን ማካተት እንዳለበት እንመለከታለን፡፡
2. እንዲጸልዩ የተጠየቁት ለጳውሎስና አብረውት ለሚያገለግሉት ነው፡፡ የጸሎት ርዕሶቹም፤ የክርስቶስን ወንጌል ማወጅ እንዲችሉ፣ እግዚአብሄር የቃሉን በር እንዲከፍትላቸውና ግልጽ በሆነ መንገድ ወንጌሉን መናገር እንዲችሉ፡፡ እኛም ከዚህ ልንማር የምንችለው አገልግሎታችንን ለመወጣት በራሳችን ብቻ እንደምንበቃ ሳናስብ የወገኖች የጸሎት ድጋፍ እንደሚያስፈልገን ያስተምረናል፡፡
3. ቁ5 እና ቁ6 ዋና ትኩረት ያደረገው በማያምኑ ሰዎች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ሁለቱን የክርስትና ህይወት ዘርፎች የሚነኩበት መንገድ፤ ቁ5 አኗኗራችን ላይ ሲያተኩት ቁ6 ደግሞ አነጋገራችን ላይ ያተኩራል፤ እነዚህ ሁለት መለያየት የማይችሉ ነገሮች ናቸው፡፡
4. በቁ7-9 የምናያቸው ቲኪቆስና አናሲሞስ ናቸው፡፡ ለሁለቱ የጋራ የሆኑት ነገሮች፤ የተወደዱ ናቸው፣ ሁለቱም ወንድም ተብለዋል፣ ሁለቱም ታማኝ ተብለዋል፡፡ የአናሲሞስ ስም ሲነሳ ምን ትዝ ይልሃል?
5. ቁ12-13 የሚናገረው ስለ ኤጳፍራ ነው፡፡ ክፍሉ ስለእርሱ የሚናገራቸው ነገሮች፡ ከእነርሱ ወገን ነው(የቆላስይስ ሰው ነው)፣ የክርስቶስ አገልጋይ ነው፣ በጸሎት ለቆላስይስ ሰዎች ዘወትር የሚጋደል ሰው ነው፣ በቆላስይስ፣ በሎዶቅያና በኢያራ ላሉት ቅዱሳን ተግቶ የሚሰራ ነው፡፡ ኤጳፍራ ለቆላስይስ ሰዎች የሚጋደልላቸው ሶስቱ ርዕሶች፤ ፍጹም እንዲጠነከሩ፣ ሙሉ ለሙሉ እንዲረጋጉና በእግዚአብሄር ፈቃድ ሁሉ ጸንተው እንዲቆሙ የሚሉት ናቸው፡፡
6. ቁ17ን ሳነብ ያስተዋልኩት ጳውሎስ የሎዶቅያ መልዕክት የሚል እንደጻፈና መንፈስ ቅዱስ ለእኛ እንዳላስተላለፈልን አያለሁ፡፡ ልክ እንደ አክሪጳ እኛም ከጌታ የተቀበልነውን አገልግሎት ከፍጻሜ ለማድረስ እንድንጠነቀቅ ያስተምረናል፡፡
7. ማርቆስ ሰላምታ እንደሚያቀርብ፣ ሰለእርሱ መመሪያ እንደተሰጣቸው፣ ሲመጣ እንዲቀበሉት፡፡ እነዚህን ክፍሎች ስንመለከት ማርቆስ አገልግሎት ጀምሮ ወደኋላ ያለ ሰው እንደነበረ፣ በኋላ ግን ቀድሞ አይጠቅምም ብሎ ለመለሰው ለጳውሎስም እንኳን ሳይቀር ጠቃሚ ሰው ለመሆን በእግዚአብሄር ጸጋ እንደበቃ እንመለከታለን፡፡ ለዚህ እንዲበቃ በመሳሪያነት ያገለገለው በርናባስ ነው፡፡
8. እያንዳንዱ የራሱን ሃሳብ እንዲሰጥና ውይይት እንዲደረግ ማበረታታት፡፡